# ግርግር ለሌባ ያመቻል

በእሳት በተቀጣጠለ ቤት ሳቢያ በሚነሳ የሰፈር ግርግር አሳቱን ለማጥፋትና እቃ ለማዳን በሚል ሰበብ ሌባ ስርን እንደሚገባና በቀውጢ ውስጥ በሚታመስ አገር ውስጥ በሚነሳ ግብግብ አጋርና ተቆርቋሪ መስሎ ለማጥቃትና የራሱን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚመጣ ጠላት እንደሚኖር ተደጋግሞ ታይቷል።ለዚህም ነው ባገራችን ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባበታል ወይም ግርግር ለሌባ ያመቻል የሚለው አባባል የተቀረጸው።

በችግር ወቅት በእውነት የሰው ልጅ ጉዳት ተሰምቷቸው የቻሉትን ለማድረግ የሚጥሩና ሌላውንም እየቀሰቀሱ ለተጎዳ እርዳታ እንዲደረግ የሚጠይቁ እንዳሉ ሁሉ ለተጎዳው አሳቢና እርዳታ አቅራቢ መስለው ለእርዳታ የተሰበሰበውን የሚሰርቁና ለራሳቸው ጥቅም የሚያውሉ ሊኖሩ እንደሚችሉ ማሰብ ብልህነት ነው።

በሕዝባዊ ትግልም ውስጥ የሕዝቡን ትግል ያበሩና የረዱ መስለው የራሳቸውን ፍላጎት ለማስከበር የሚራወጡ እንደማይጠፉ በተደጋጋሚ ታይቷል፤አሁንም እየታዬ ነው።በአለፉት ዓመታት የኢትዮጵያ ሕዝብ በገጠመው ችግር ጀርባ የተጠቀሙ እንዳሉ አይዘነጋም።ተደጋግሞ በተከሰው ድርቅ ምክንያት ሕዝብ ለርሃብና በሽታ ተጋልጦ እንደቅጠል ሲረግፍ በዚያ ተገን እርዳታ የሰጡ መስለው የተሰጠውን እርዳታ ለግላቸው ያዋሉ ግለሰቦችና ድርጅቶች እንደነበሩ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፤ አሁንም መኖራቸው አይካድም።

የ 1964-66 ቱ የድርቅ መቅሰፍት ጠባሳው ሳይደርቅ ታሪክ እራሱን ይደግማል እንደተባለው ከአስር ዓመት በኋላ የዛሬ ሰላሳ ሁለት ዓመት በ 1974-76 እ.ኢ.አ. (በፈረንጆቹ 1984 ዓ.ም.)በአገራችን ከፍተኛ የድርቅ መቅሰፍት እንዳለ ይፋ በወጣበት ጊዜ በስልጣን ላይ የነበረው የደርግ ስርዓትም ለዚያ የሚሆን ቅድመዝግጅት ባለማድረጉ የብዙ መቶ ሽህ ሕዝብ ህይወት እንደጠፋ የምናውቀውና ለወደፊቱም ታሪክ መዝግቦ ያስቀመጠው ኢትዮጵያውያንን እስከዛሬ ድረስ ለሃፍረት የዳረገ ሁኔታ ነበር።

በዚያን ጊዜ ለተቸገሩ ወገኖቻችን እርዳታ እንሰበስባለን ብለው የተነሱ ብዙ የውጭአገር ድርጅቶችና ኢትዮጵያኖች በያሉበት ተንቀሳቅሰው ነበር።በውጭ አገር ከተነሳሱት ድርጅቶች መካከል ሻእቢያና ወያኔ በጫካ በነበሩበት ጊዜ ከጎናቸው በመቆም እርዳታ ሲያደርጉ የነበሩ በሃይማኖትና በሰብአዊ ሙብት ድርጅት ስም የሚንቀሳቀሱ አውሮፓውያን ነበሩ።

እነዚህ ድርጅቶች በዚህ የድርቅ እርዳታ ሰበብ ከሕዝብ የተሰበሰበውን እርዳታ ብዙውን ድርሻ በሥራ ማስኪያጀና በመሳሰሉት ወጭዎች ሰበብ ለራሳቸው ገቢ ሲያደርጉ የተረፈውን ለሚረዷቸው ተገንጣይ ሃይሎች የጦርነት ባጀት መሟያ አድርገውታል። ለተራበው ሕዝብ ተላከ የተባለው እርዳታም በአገራቸው ፋብሪካ በገፍ ተዘጋጅቶ ለገበያ ቀርቦ ገዥ ያጣ፣ደረቅ እሽግ የከፉ ቀን ወይም የጦር ሜዳ ምግብ ነበር።ከአውሮፓ የተላከውን እርዳታ ከቦታው ለማድረስም የአውሮፓውያኑ የመርከብና የአውሮፕላን አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ተጠቅመዋል።ይህን ከፍተኛ ወጭ ለማዳንና ሕዝቡም የለመደውን እህል እንዲመገብ፣የቀረበላቸውን ሃሳብ አልተቀበሉትም።የቀረበው ሃሳብ በአጎራባች አገሮችና በሌላው የኢትዮጵያ ክፍለሃገር የሚመረተውን ገዝቶ በማቅረብ ለተቸገረው በቅርበትና ባስቸኳይ እርዳታው ሊደርስ ይችላል የሚል ነበር።

በተጨማሪም አስቸኳይ እርዳታ ከማድረጉም ጎን ለጎን ለወደፊቱ ድርቅ ቢከሰትም እርሃብ ዳግም እንዳይከሰት በሚረዳው መልኩ ገንዘቡ ጥቅም ላይ ይዋል የሚል ሃሳብ ተሰንዝሮ ነበር።ሆኖም ግን የታያቸውና የዘረጉት እቅድ በእርዳታ ስም በተዘዋዋሪና በቀጣይነት የሚጠቀሙበትን በመሆኑ ለቀረበላቸው አስተያየት ትኩረትም አልሰጡትም።

ከሕዝቡ የተሰበሰበው በሙቶ ሚሊየን የሚቆጠረው ገንዘብ በሃይማኖት ተቋማት፣በካቶሊክና በፕሮቴስታንት እንዲሁም መንግሥታዊ ባልሆኑት ድርጅቶች(NGO)ካዝና ውስጥ ገብቶ ለፈለጉት ተግባር አውለውታል።በደሃው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ዕቅዳቸውን አሳኩበት፤ተገንጣዮችንና አስገንጣዮችን አጎለበቱበት።የካቶሊክ ተቋማቱ ከታሪካዊ ትስስራቸው የተነሳ ከተገንጣዮች ጋር የነበራቸው ግንኙነትና የሰጡት እርዳታ የሚገርመን ባይሆንም በዚህ በሰዎች ህይወት ጀርባ የተከናወነው ሸፍጥና ዘረፋ በደሃው የትግራይ ሕዝብ ስም ጭምር የተደረገ በመሆኑ እራሳቸው ለትግራይ ሕዝብ መብትና ነጻነት እንታገላለን ብለው የተነሱትም አሁን በሥልጣን ላይ የተቀመጡት የህወሃት አባላት ተቋዳሾች በመሆናቸው የወንጀሉ ተካፋዮች ነበሩ።

በካቶሊኮቹ ብቻ ሳይሆን በፕሮቴስታንቱም በኩል እንዲሁ በኦሮሞ ነጻ አውጭ ድርጅት በኩል የተደረገው እርብርቦሽ ያንኑ የሚመስል ነበር። አሁንም ቢሆን በዚያው ቀጥሎበት ይገኛል። በይበልጥ ቅስም የሰበረው ደርግ አስረኛ ዓመቱን ለማክበር ሲል በዚያ በፈታኙና ቀውጢ ሰዓት በሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር ወጭ አውጥቶ ድል ያለ ፌስታ ማዘጋጀቱ ነው።ምንም እንኳን ሃላፊነት የነበረውና ለሕዝብ የሚጨነቅ አለመሆኑ ቢታወቅም በመንግሥት ደረጃ ያለ አካል አገሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ በርሃብ ታውቆ የውጩ ሲረባረብ ያንን ያህል ክህደትና ጭካኔ የተሞላበት ምግባር ላይ መዋሉ እስከሙቼውም በታሪክ ይቅርታ የሚባልለት አይደለም።ያም ብቻ ሳይሆን በሚገቡ የእርዳታ ስጦታዎች ማለትም በምግብ፣በመድሃኒትና በገንዘብ ላይ ቀረጥ በማስቀመጥ ከፍተኛ ገንዘብ ሰብስቦ ለጦር መሳሪያ ግዥና ለባለሥልጣኖቹ ኪስ ማብቃቱም ሌላው አሳፋሪና ኢሰብአዊ ምግባር ነበር።

በስደት በሚኖሩ ኢትዮጵያኑም ዙሪያ ይህንኑ የመሰለ አውሬነትና እራስ ወዳድነት የተንጸባረቀበት ሁኔታ ነበር።እኔ የማውቀውን ብናገር፤በሆላንድ ውስጥ የነበርነው የደረሰውን ችግር በሚመለከት የሚቻለንን ለማድረግና እርዳታ ለመሰብሰብ ስንነሳ በተጓዳኝ ሌሎች ጥቂት ኢትዮጵያውያን እንዲሁ እርዳታ እንሰበስባለን ብለው ተነሱ።ተቀራርቦ ለመስራት የተደረገው ጥረት ሳይሳካ በተነሱበት መንገድ ቀጥለው በተለይም ሁለቱ ኢትዮጵያውያን ከአገሩ ዜጎች ጋር የተጋቡ በመሆናቸው የደቹን ህብረተሰብ ለመሳብና ለማሳመን በመቻላቸው ሌሎቻችን ከሰበሰብነው በላይ ገንዘብ ለመሰብሰብ ቻሉ። በእኛ በኩል የሰበሰብናትን በድምጽ ብልጫ ውሳኔ ተወስኖ ያደርስልናል ለተባለው ድርጅት ተሰጠ።

በሌሎቹ በኩል ግን “ሌባ ሲሰርቅ ይስማማል ሲካፈል ይጣላል” እንደሚባለው ሆነና በክፍፍሉ ላይ ጭቅጭቅ ተነሳ፤መፈነጋገል ተጀመረና ግብግብ ገጠሙ። አንዱ በራሱ ስም መኪና ገዛበት፤ይኸው ሰው ከሌላው ጋር በድራግ ሱስ የተለከፈ ስለነበር በዛው በድራግ ግዢ ገንዘቡን አባከኑት።ሌላው የዋህ ብቻውን አጨብጭቦ ቀረ።ቢወጣ ቢወርድ የሚሰማው አጣ።

የሚገርመው ነገር፣በድሆቹ ስም ይህን ያደረጉት ሰዎች አንዳቸውም አልተባረኩም፤ሁለቱ ለጡረታ ሳይበቁ በድንገተኛ በሽታ ሞቱ፤ አንዱም ኑሮ ሳይሳካለት ቀረና የወለደውን ልጅ ስሞ ሳይጠግበውና ለቁም ነገር ሳያበቃው አገር ጥሎ ጠፋ። በእብሪት ተነፍቶ የነበረው ደርግም ቅሌት ተከናንቦ ፈራረሰ።የኢትዮጵያ ሕዝብ እምባ በከንቱ ደርቆ አይቀርም፤ ይዋል ይደር እንጂ ግፍ የሰሩበትን ዋጋ ያስከፍላል።

ይህንን እንደምሳሌ ያቀረብኩት አሁን ኢትዮጵያ ባለችበትና ሕዝብ በሚሳተፍበት ትግል ዙሪያና በእርዳታ ስም በመከናወን ላይ ያለው የመሸቀዳደምና በስም የመነገድ ምግባር በመከሰቱ ከዚህ አይነት ደረጃ ላይ ሊደርስ እንደሚችል በመገመት ነው።

ሕዝብ ለዴሞክራሲ ስርዓት መስፈን፣ለሙብቱና ለአገሩ አንድነት በሚዋደቅበትና መስዋዕት በሚከፍልበት በአሁኑ ጊዜ በልዩ ልዩ ስም ትግሉን እንመራለን፣ እንረዳለን፣የትግሉ አጋርና አካል ነን፡ የሚሉ ተነስተው የሚያደርጉት ሽኩቻና መስገብገብ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ በማጤን በአፋጣኝ እንዲወገድ ለማሳሰብ ነው።

ሕዝቡ ኢትዮጵያ ወይም ሞት ብሎ በአንድ ሰንደቅ ዓላማ ስር ተሰልፎ ሲታገል የዚያ ተጻራሪ የሆነ የመገንጠልን ቅኘት የሚቃኙና የነሱን ጥቅም ለማስጠበቅ የተነሱ አስመሳዮች ይህን የሕዝብ ትግል ቀልምመው ለራሳቸው ፍላጎት ለማዋል የሚቅበጠበጡ ስላሉ ከሚያደርጉት ጸረ ኢትዮጵያ እንቅስቃሴ እንዲታቀቡ ማስገደድና ለነሱም እርዳታም የሚያደርጉ የዋህ አገር ወዳዶች ሁኔታውን እንዲያጤኑት ለማሳሰብ ነው።አንዳንዶቹ ድርጅቶች እነሱ የማይቆጣጠሩት ህዝባዊ እንቅስቃሴና ትግል ቢሰናከል ይመርጣሉ።ለእነሱ ትግል ማለት ለተነሱበት የማይታወቅ ዓላማ ማንብደድና የጠየቁትን ድጋፍ ሳይጠራጠሩ መስጠት ነው።

አፍ አላቸው ያምታታሉ፣የሰውን ደካማ ስነልቦና ፈልቅቀው ስለሚያውቁ ይጠቀሙበታል።በዘፈኑ፣በትያትሩ፣በቀልዱ፣በከባቢ ስሜቱ፣በጥቅም ሰንሰለት ተብትቦ በማሰር… የሚቃወማቸውን በማስፈራራቱና በሃሰት ስብእና በሚነካ ዘመቻ የፈለጉትን ከማድረግ አይመለሱም፤በተወሰነም ደረጃ ተሳክቶላቸዋል። ግን አብሯቸው ማምሸቱ ያጠራጥራል።የጊዜ ጉዳይ ነው ይጋለጣሉ።

ጎን ለጎንም በራሱ ሃይል ተነሳስቶ ትግል በሚያደርገው ሕዝብ ስም፣በተለይም በአማራው ማህበረሰብ ስም ሞረሽ ፣ቤተአማራ፣ዳግማዊመአድ…ወዘተ የተባሉ እርስ በርሳቸው የሚሻኮቱ የተለያዩ ድርጅቶች አቋቁመው የገንዘብ እርዳታ በመሰብሰብ ላይ የተሰማሩ ቡድኖች ተመስርተዋል። አነሳሳቸው ቀና ቢመስልም በዚህ መልክና ብዛት ስር የሚያደርጉት ተለያይቶ ጉዞ ወደፊት ሊያስከትል የሚችል ችግር እንዳለ ይሸተኛል።ያ ከመሆኑ በፊት አደጋውን ተገንዝበው እውነት ለአማራው ማህበረሰብ ካሰቡና ከተጨነቁ በአንድ ነጠላ ድርጅት ስር ተሰልፈው የሚገኘውን እርዳታ በሚፈለገው ቦታ ለሚፈለገው ተግባር እንዲደርስ ቢያደርጉ የሚያስተማምንና ውጤት ያለው ጥረት ይሆናል።

በየአቅጣጫው የሚገኘው የእርዳታ ገንዘብ ለምን ተግባር መዋል እንዳለበት በግልጽ መቀመጥ አለበት።ለትግል ማስኬጃ፣ለመደራጃ፣ለመጓጓዣ፣ለቆሰለው ህክምና፤ ለምግብ፣ ለሰላማዊ ሰልፍ ዝግጅት፣ለታሰሩት ስንቅና ጠበቃ፣ ለተሰዉት ቤተሰቦች እርዳታ፣ወላጅና እረዳት ላጡት መደጎሚያ፣ለተፈናቀሉት መቋቋሚያ …ወዘተ የሚውል መሆኑን ለይቶ አላፊነቱን የሚወስደው አካል ቢታወቅ እረጅው ለፈለገው ተግባር ለመርዳት ይቀለዋል።

በጥቅሉ እርዳታው ተሰብስቦ ከምን ቦታ ላይ እንደሚውልና ተጠያቂው ማን እንደሆነ ካልታወቀ የረጁን እምነት ያሳጣል። በፖለቲካው ዙሪያ በሚደረገው የተለያየ ትግልና በሰብአዊው በንገድ የሚደረገው የእርዳታ እርብርቦሽ ተለይቶ ቢቀመጥ መልካም ይሆናል። በፖለቲካ ትግል ለተሰማሩት እርዳታ የሚሰበስብ አካል ለብቻው መንቀሳቀስ ይገባዋል እንጂ ከሕዝቡ ጉዳት ጋር በተያያዘው ሰብአዊ እርዳታ የማሰባሰብ እንቅስቃሴ ውስጥ ባይጣመር የተሻለ ነው።ለሰብአዊው እርዳታ የሚያሰባስበው ቡድን ከሁሉም የተውጣጣ ሕዝባዊ አካል ተጠያቂነቱም ለሕዝቡ ሲሆን ለፖለቲካ ድርጅቶች ግን የራሱ አባላት የሚመሩትና ተጠያቂነታቸውም ለፖለቲካ ድርጅቱ ይሆናል።

በጣም የሚገርመው ደግሞ በአሁኑ ጊዜ ይባስ ብሎ እርዳታ አሰባሰቡ እንደፖለቲካው አለሰላለፍ ጎጥ እየያዘ መምጣቱ ነው።የጎጃም፣የወሎ፣ የጎንደር፣የሸዋ…እያለ መሰባሰብ እንደተጀመረ ይፉ ይነገራል።ይህንን አይነት አደረጃጀት የምንታገለው ወያኔ በደስታ ይቀበለዋል፣ያበረታታዋልም።በዚህ በየአቅጣጫውና በየስሙ በሚገኘው እርዳታ ምክንያት አላስፈላጊ ግጭትና ክፍፍል እንዳያመራ በኢትዮጵያውያን ስም በተከፈተና የጋራ ቁጥጥር ወዳለበት አንድ የባንክ አካውንት ቢገባ የተሻለ ከመሆኑም በላይ እረጁን እምነት እንዲያድርበት ያደርጋል፤ለተረጂም የሞራል ብርታት ይሰጣል።ትግሉንም አገር አቀፍ ያደርገዋል።

ተለያይቶ በየአቅጣጫው መባከን ሃይልን ማመንመን ሲሆን በከባቢ ስሜትና ጎጥ መሰለፍ ደግሞ ትልቁን የኢትዮጵያዊነትን መንፈስ ይሰብራል፣ሃይልን ይንዳል፣የአገርንም አንድነት ያናጋል፤አካሄዱም ከሚታገሉት የወያኔ አካሄድ አይለይም፤ የሱኑ ጉዞና መንገድ መከተል ይሆናል። በየቦታው በተለይም በአማራው ክልል ከተንጸባረቀውም ሕዝባዊ ትግል መልእክትና አቋም የተለየና ተጻራሪ ነው።አሁን በየቦታው የሚካሄደው ሕዝባዊ ትግልና አመጽ ኢትዮጵያዊነትን የሚያጎላ ነው።በአንድ ኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም ቦታ የሚካሄደውን ሕዝባዊ ትግል ለማገዝና የሚደርሰውን ጉዳት ለመታደግ በየጎጡ መደራጀት አስፈላጊ አይደለም።

የሕዝቡንም ጉዳት ለመታደግ በፖለቲካ ድርጅታዊ ጥቃሞት አንጻር እየታዩ መደረግ አይገባውም። የህዝብ ጉዳት የፖለቲካ ድርጅቶች ሽቀጥ የሚሸጡበት ሱቅ አይደለም። በሃቅ ችግሩን ለመታደግና ለሕዝቡ ለመድረስ ከተፈለገ አንድ ወጥ የሆነ፣ከፖለቲካ ድርጅቶች፣ከእምነት ተቋማትና ከአካባቢ ጎጠኛ አስተሳሰብ ተጽእኖ ነጻ የሆነ በኢትዮጵያዊነት መንፈስ የተዋቀረ ብሔራዊ እርዳታ አስተባባሪ አካል(National solidarity coordinating body) በዓለም አቀፍ ደረጃ አቋቁሞ መንቀሳቀሱ ይበልጥ አስተማማኝ ይሆናል። በመንቀሳቀስም ላይ ያለው

ሎባል አሊያንስ(Global alliance)የተባለው አሰራሩን ከፖለቲካ ድርጅት ትስስርና ዝንባሌ አጽድቶ ቢንቀሳቀስ የበለጠ ሊጠቅም ይችላል። እንደኔ ያለውን ለመርዳት የሚፈልግ ዜጋ ከመርዳት የሚያግደው ነገር የድርጅቶች ጋጋታ መኖር ነው።ይህ አይነቱ አሰራር ቢቀር መልካም ነው።

ወያኔ ያደረሰውና የሚያደርሰው ጥቃትና ጉዳት ጎሳና ቦታ የለዩ አይደለም።ይህን የጋራ ጥቃት በጋራ ሆኖ መቋቋምና ማሶገድ ተገቢና አስፈላጊ ነው።ከዚህ የተለዩ ሌላ አማራጭ የለም።ቢኖርም ውጤቱ የሚያረካ አይሆንም።እስካሁን የሚታገለውን ሕዝብ ለሚገጥመው ችግር ለመርዳት የተደረገውና ለመደረግም የታሰበውን ጥረት እያደነኩኝ ወደ መጥፎ አቅጣጫ እንዳያመራ በቅድሚያ እንዲታሰብበት ለማስገንዘብ ያቀረብኩት ይህ ሃሳብ በየፊናው በቀናነት የሚደረገውን የህዝቡን ተሳትፎና ጥረት ለመቃወም ሳይሆን ከአውሬዎች መንጋጋ ለመከላከል ወይም የእርስ በርስ ግጭትና ንትርክ ውስጥ ሳይገቡ አመርቂ ውጤት እንዲያመጣ ካለኝ ቅን ምኞት በመነሳት እንደሆነ እንዲታወቅልኝ አሳስባለሁ።ብዙ ስብስቦች በገንዘብና በቡድናዊ ስሜት ምክንያት ከመፈራረስ ደረጃ ላይ እንደደረሱና በደጋፊው ላይ ተስፋ መቁረጥን እንዳስከተሉ ያየሁ በመሆኑ ያ በድጋሚ እንዲከሰት አልሻም።

ማሳሰቢያ

አሁን አገራችንና ወገናችን ያለበት ወቅት ወሳኝ ደረጃ ላይ ደርሷል።ሕዝብ ከመንግሥት ጦር ጋር ተፋጧል፣እየተፋለመ ነው።ብዙ እልቂት ሊከሰት ይችላል፤ አሁንም እየተከሰተ ነው።የእርዳታ ያለህ ብሎ ይጣራል።የወገኑና የሃገሩ ጉዳይ የሚያሳስበው ሁሉ ለዚህ ጥሪ በያለበት መልስ ሊሰጠው ይገባል፣ከከባቢ እስከ ቤተሰብ ድረስ የገንዘብ እርዳታ ማሰባሰብ ይኖርበታል።የኮሚኒቲ ማህበራትም በአካባቢያቸው የሚኖረው ኢትዮጵያዊው

ተገናኝቶ የሚችለውን ያህል እርዳታ እንዲያደርግ የአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ(Emergency call) ማድረግ ይኖርባቸዋል። የሚሰበሰበውን ገንዘብ በተናጠልና በየጎጡ ለሚንቀሳቀሱትም ሆነ ለፖለቲካ ድርጅቶች ማስረከብ ሳይሆን በአገር አቀፍ ደረጃ ተቋቁሞ ለሚንቀሳቀሰው አካል ማስተላለፍ ይኖርበታል።ከተቻለም በሚመጣው የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ወይም የመስቀል ዕለት በዓል ጋር የተያያዘ ዝግጅት በማድረግ ጎላ ያለ ገቢ ማሰባሰብ የሚቻልበት መንገድ ሊታሰብ ይገባል። በነዚሁ ቀናቶች በየአገሩ የሚኖሩት የኪነት ባለሙያዎች ተባብረው ለዚህ ህዝብና አገር አድን ዘመቻ ቅድሚያ በመስጠት ብሔራዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ በዚህ አጋጣሚ ጥሪየን አቀርባለሁ።

በአንድነት ለአንድነት!

አገሬ አዲስ

http://www.ethiopanorama.com